# የገበያ ኢኮኖሚ ወይስ ካፒታሊዝም ፣ ወይስ ሌላ ...

## -የኢኮኖሚው ጉዳይ አጥጋቢ መልስ ያስፈልገዋል-

### መግቢያ

„ ለምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው“ የሚለውን በቅርብ ያወጣሁትን ጽሁፍ አስመልክቶ ከየአቅጣጫው ብዙ ጥያቄዎችና ትችቶች ደርሰውኛል። አንዳንዶቹ የኢትዮጵያን የተወሳሰበና የግሎባል ኢኮኖሚን ስንመለከት ፣ ኢኮኖሚና የነፃ ገበያ የሚባሉት ጽንሰ-ሃሳቦች ትርጉም እየተምታቱብን መጥተዋል። ስለዚህም በነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ የጠራ አስተሳሰብ እስከሌለ ድረስ እኛም ላለው ምስቅልቅል ሁኔታ ተጨማሪ አስተዋጽኦ ማበርከታችን አይቀርም የሚል ነው። ሁለተኛው ጥያቄና ትችት ደግሞ ፣ በነፃ ገበያና በካፒታሊዝም መሀከል ያለው ልዩነትና ግኑኝነት ግልጽ አይደለም የሚል ነው። ይህም ጉዳይ በበቂው መተንተን ያለበት ነው የሚል አዎንታዊ ትችት ነው። በሶስተኛ ደረጃ ፣ ኒዎ-ሊበራሊዝም እየተባለ ሲጻፍና ሲወራ እንሰማለን ፤ ለአሁኑም የፊናንስ ገበያ ቀውስ ተጠያቂ እንደሆነ ይነገራል። ለመሆኑ ይህ ጽንሰ-ሃሳብ ከካፒታሊዝም ወይም ከገበያ ኢኮኖሚ ጋር የሚያገናኘው ነገር ምንድ ነው? ለምንስ ለቀውሱ እንደምክንያት ይነገራል? አራተኛ ፣ ስለኢኮኖሚ በምትጽፍበት ጊዜ አቋምህን ለመረዳት ተቸግረናል። አንዳንድ ጊዜ የግራ መሰል አስተሳሰብ ያለህ ይመስላል ፤ እዚያው በዚያው ደግሞ ካፒታሊዝምን ልናልፈው የምንችለው ስርዓት አይደለም ትላለህ። አቋምህ ቢብራራ ጥሩ ነው የሚል ትክክለኛ ትችትና ጥያቄ ቀርቧል። በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ ፣ በምዕራቡ ዐለም ግሎባላይዜሽንና የገበያ ኢኮኖሚ አጠያያቂ በሆነበት ወቅት እኛ በበኩላችን የግዴታ የገበያ ኢኮኖሚን ተግባራዊ ማድረግ አለብን እያልን እንጮሀለን። ለምን ለራሳችን የሚበጅ የስልጣኔ ፈለግ አንፈልግም በማለት ተገቢ አስተያየትና ጥያቄ ሰንዝረዋል። ከበድ ያሉ ትችቶችና ጥያቄዎች ናቸው ማለት ነው። ሰፊ ሀተታንና መልስን የሚሹ ግሩም ጥያቄዎች ናቸው። በቅደም ተከተል ለመመለስ እሞክራለሁ።

ከዚህ በተረፈ ጽሁፌን በሚመለከት አንዳንዶች ወደ ማኩረፍ አምርተዋል። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር አለ። በመጀመሪያ የአንድ አገር ጉዳይ የጥቂት ያገባናል ባዮች ጥያቄ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብና ፣ በተለይም ደግሞ የጠቅላላው ምሁር ነኝ ባይ ጥያቄ ነው። ስለዚህም ፣ ሁሉም በሚችለው መልክ አስተያየቱን መስጠት ይችላል። ማንም ሰው የሃሳብ ገደብ ሊያደርግ አይችልም። ሁለተኛ ፣ የግዴታ ሆኖ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የዕድገትን ፈለግ በሚመለከት የተለያዩ አቋሞች ይኖራሉ። ስለዚህም ፣ እኛም ሳንወድ በግድ የተወሰነ አመለካከትን እናስተጋባለን። በዐለም ላይ የተነዙት ርዕዮተ-ዓለሞችና ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች የኛንም ጭንቅላት ጠምደው ጭንቀት ውስጥ ከተውናል። የትኛው ነው ትክክለኛው የህብረተሰብ ግንባታ ዘዴ ለሚለው መልስ የምንፈልግ ጥቂት አይደለንም። ሶስተኛ ፣ በፖለቲካ ትግል ውስጥ እሳተፋለሁ ብሎ የተነሳና የሚነሳ ሁሉ አንድ ሃሳብ ሲሰነዝር እሱን የሚቃወምም እንደሚወረወር መረዳት አለበት። ማንኛውም ግለሰብ ምሁር ሰለሆንኩ እኔ የምጽፈው ብቻ ትክክል ነው ብሎ ተዝናንቶ ሊቀመጥ አይችልም። ለሚቀርብለት ጥያቄም ሆነ ትችት ተዘጋጅቶ መጠበቅ አለበት። መደናገጥና ወደ ቂም በቀል ማምራት የለበትም። ለትችት ዝግጁ የሆነ ሰው ብቻ ህብረተሰብአዊ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

በዚህ ጸሀፊ ዕምነት አሁንም ቢሆን በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ውይይትና ክርክር ብቻ ነው አንድን አገር ነጻ ሊያወጣ የሚችለው። የሶስት ሺህ ዐመት የአውሮፓ ታሪክ የሚያረጋግጠው ይህንን ነው። ስለዚህም ፣ ለማንኛውም ህብረተሰብአዊ ጥያቄና ፕሮጀክት የግዴታ ክርክርና ውይይት ያስፈልጋል። ካለበለዚያ በዲሞክራሲና በነፃ ገበያ ስም ብቻ የሚደረግ ብልቅ ጥልቅ የሚል አስተያየት መንገዱን ለአምባ-ገነኖች የሚያመቻች ይሆናል። ወደ ቁም ነገሩ ከማምራቴ በፊት ለትችቱም ሆነ ለጥያቄው የመልስ መሰረት ወደ ሆነው የቲዎሪንና የርዕዮተ-ዓለምን ጥያቄ ወይም አስፈላጊነት እያነሳን እንወያይ።

# የርዕዮተ-ዓለምና የቲዎሪ አስፈላጊነት

በአውሮፓ የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ የሰውን ልጅ ሚናና የአስተሳሰብ ፍልቀት በሚመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ የአመለካከት ትግል መደረግ የተጀመረው በግሪክ ስልጣኔ ዘመን ነው። በዚያን ጊዜ የተደረገው ክርክር በቀጥታ የዚህኛውን ወይም የዚያኛውን መደብ ጥቅም አስጠብቃለሁ በሚል የተነሳ በሁለት ምሁራን ክንፍ መሀከል የተደረገ ክርክር ሳይሆን ፣ ዋናው የዕውቀት ምንጭ ምንድ ነው በሚለው ላይ ያተኮረ ነበር። በሶክራተስና በፕላቶን የሚመራው ክንፍ ፣ የዕውቀት ምንጩ አርቆ ማሰብና እየመላለሱ መጠየቅ ነው ሲል ፣ ሶፊስቶች ደግሞ የዕውቀት ዋናው ምንጭ ይህ ሳይሆን ፣ ተጨባጭ ነገር ወደ ጭንቅላታችን ውስጥ ሲገባ ከዚህ በመነሳት የምንሰጠው ትንተና የዕውቀት ምንጭ ነው ብለው ይከራከሩ ነበር። በዕውቀት ላይ የተደረገው ውይይት ወደ ህግም በመተላለፍ ፣ እነ ፕላቶን የተፈጥሮን ህግ የህብረተሰብ መተዳደሪያ ደንብ ነው ብለው ሲከራከሩ ፣ ሶፊስቶች ደግሞ ይህ ሊሆን አይችልም ፤ ስለዚህም አንድ የገዢ መደብ ራሱ ፈቅዶ የሚያወጣው ህግ(Positive Law) ተግባራዊ ሲሆን ፣ ይህ ህዝብ የሚተዳደርበት ህጋዊ መሰረት ነው ብለው ይከራከሩ ነበር።

ይህንንና ፣ የዕውቀትን ምንጭ በሚመለከት በተለይም ከአስራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እንደገና በጠለቀ መልክ ሲካሄድ ፣ ዋናው ዓላማው ለሳይንስ የሚያመቸውን መንገድ ለመፈለግ የተደረገ ጥልቀት የነበረው ውይይት ነበር ። በአንድ ነጠላ ነገር ላይ አትኩሮ ከዚያ ወደ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ መድረስ(inductive/deductive method) ፣ ወይም ደግሞ ከአጠቃላይ ሁኔታ ተነስቶ ቀስ በቀስ ወደ ተናጠል ጉዳይ ላይ መድረስ (deductive/inductive method) የሚለው የአተናተን ዘዴ ሲያከራክር ኖሯል።በተለይም በዴስካር(Descartes) የዳበረው ያሰራር ዘዴ ፣ ማለትም በተጨበጠ ነገር ላይ ማትኮርና ከተወሳሰቡ ነገሮች ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን ነጥሎ በማውጣት በሱ ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር ማድረግ በአውሮፓ የምሁር እንቅስቃሴ ውስጥ በአሸናፊነት የወጣና ኢምፔሪሲስታዊ ለሆነ ሳይንሳዊ ጥናት መሰረት የጣለ ነው። በዚህም ምክንያት ፣ ይህ ሳይንሳዊ የአተናተን ዘዴ በአሸናፊነት መውጣት የአውሮፓ ማህበረ-ሰብ ቀደም ብሎ ከነበረው የካቶሊክ ሃይማኖት አስተሳሰብ በመላቀቅ ወደ ተጫበጭ ሀብትን(Material Wealth) ማዳበር የቻለበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ-ዘመን እንግሊዝ በኢኮኖሚ ፣ በሚሊታሪና በፖለቲካ የበላይነትን ስትቀዳጅ ፣ የርዕዮተ-ዓለም ሚና የበለጠ እየጎላ ይመጣል። ስለሆነም ፣ የህብረተሰብ አደረጃጀት ግልጽ እየሆነ ሲመጣ ፣ የዚህኛውን ወይም የዚያኛውን መደብ ጥቅም የማስጠበቅ ጉዳይም ጉልህ እየሆነ ይመጣል። ይህ ደግሞ በቀጥታ በዚያን ጊዜ በግልጽ የሚታየውን የኃይል አሰላለፍ የሚያንጸባርቅ ሲሆን ፣ በግል ሀብት ጥያቄና በሀብት ክፍፍል ፣ የሀብትን ምንጭ በሚመለከትና የብዝበዛን ጥያቄ ጎላ አደርጎ በማንሳት ነበር። ይሁንና ፣ ርዕዮተ-ዓለምን ብቻ ሳይሆን ዕሴትንም በሚመለከት በአውሮፓ ምድር ውስጥ በተለያዩ የህብረተሰብ ጥያቄዎች ዙሪያ ትግልና ክርክር ተካሂዷል። ይህም ማለት ፣ አንዳንዶቹ ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ትግሉ በግራዎችና በቀኞች መሀከል የተደረገ ብቻ ሳይሆን ፣ ለሃይማኖትና ለሰብአዊነት መከበር የቆሙ ምሁራንንም ያካተተ ሰፋ ያለ የአመለካከት ትግል ነው። ዛሬ የሚነሳውም ክርክር ንጹህ የርዕዮተ-ዓለም ትግል ሳይሆን ፣ መሰረታዊ የዕሴት ጥያቄን ያካተተና የኑሮንም ትርጉም እንድንጠይቅ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ንጹህ የርዕዮተ-ዓለም ትግል ብቻ ዋናው የአመለካከት መሰረት መሆኑ ቀርቶ በሰብአዊነት ላይ ያተኮረና ሰፋ ያለ የስልጣኔን ትርጉም የሚያካትት ፣ በመኖርና ባለመኖር መሀከል የሚደረግ ትግል ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ በላይ በአጭሩም ቢሆን የተቀመጠውን በአውሮፓ ምድር የተካሄደውን ጠለቅ ያለ የምሁር እንቅስቃሴ ወደ ጎን በማድረግ በአሸናፊነት የወጡ ኃይሎች የአንድ ህብረተሰብ ዕድገት በተወሰነ የርዕዮተ-ዓለም ክልል ብቻ እንዲሽከረከርና ህብረተሰቦችም ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ፣ እንዲያም ሲል ሰፋ ላለ ወደ ውስጥ ያተኮረና የአንድን ህዝብ የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሰፋ የሀብት ክምችትና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዳይካሄዱ ለማገድ ቻሉ። በዚህም ምክንያት ለብዙዎቻችን ግልጽ ያልሆኑና የሚያወናብዱ ነገሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ በመስፋፋት ለዚህኛው ወይም ለዚያኛው ርዕየተ-ዓለም ሰለባ ለመሆን በቃን። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ዓለም በሁለት ካምፕ ነው የተከፈለችው በማለት የተስፋፋው ቅስቀሳ ብዞዎቻችንን ማወናበድ ችሏል። በተለይም አሜሪካን የበላይነቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት የተጠቀመበት የርዕዮተ-ዓለም ቅስቀሳ ብዙዎቻችን

ማንነታችንን እንድንስትና ለአንድ አፍታ እንኳ ቆም ብለን ለመጠየቅ ያልቻልንበት ደረጃ ለመድረስ በቅቷል። „ሁለት ዝሆኖች ሲራገጡ ሳሩ ነው የሚጎዳው“ እንደሚሉት አነጋገር ፣ ሁለት ኃያላን መንግስታት በፈጠሩት ርዕዮተ-ዓለምና ግብግብ ውስጥ በመግባት ኃይላችንና ሀብታችንን ለማጥፋት በቃን። ዛሬም ያለው ችግር የአንድን ህብረተሰብ ዕድል ከአንድ ሁኔታ ብቻ ለመረዳት መጣርና ሽንጥን ገትሮ ወደ ፊት ለመሽምጠጥ መሞከረ ነው። የነገሮችን ውስብስብነት ፣ በተለይም ቀና መስሎ ግን ደግሞ ርዕዮተ-ዓለምን ሽፋን አድርጎ የሚደረግን ትግል ጠጋ ብለን ለመመርመር ያለን ኃይል በጣም እየቀነሰ መጥቷል ብል ስህተት አይሆንም። ዛሬ በአሜሪካን የጤንነት ደህንነት ፖሊሲን አስመልክቶ በሪፓብሊካኖችና በዲሞክራቶች መሀከል የሚደረገው ትግል የቱን ያህል የሰው ልጅ የመኖርና ያለመኖር ዕድል በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ጥላ ስር እንደሚወሰንና በውሸት ቅስቀሳ አብዛኛውን ህዝብ ማሳሳት እንደሚቻል ነው የሚያረጋግጠው። 47 ሚሊዮንን ህዝብ በፖሊሲው ተጠቃሚ ለማድረግ በፕሬዚደንት አባማ የቀረበው ዕቅድ ከሪፓብሊካኖችና ብሉ ዶግስ(Blue Dogs) ተብለው በሚጠሩት 50 ያህል ዴሞክራቶች ተቃውሞ የደረሰበት ፣ ሁለቱም ኃይሎች የፋርማሲ ኢንዱስትሪንና የኢንሹራንስ ኩባንያን ጥቅም አስጠባቂዎች መሆናቸውን ነው የሚያሳየው። ግልጽ እስካልሆነ ድረስ እንደዚህ ዐይነቱ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብን ያዘለ የሚመስል ፣ ግን ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም የተሸፈነ ስሌት ወደ ፊት ወደኛ ጋ በመዛመት ህብረተሰብአዊ ውዝግብ እንደሚያስከትል መገንዘቡ ከባድ አይሆንም።

በኛ ዘንድ ያለው ችግር አንድን ነገር እንደ ጨለማና ብርሃን በመውሰድ ፣ አንድ ህብረተሰብ ንጹህ ርዕዮተ-ዓለም የሚካሄድበት በግራዎችና በቀኞች መሀከል የሚደረግ ሽኩቻ ሆኖ መወሰዱ ነው። በዚህም መሰረት በዓለም ላይ እስካሁን ድረስ የተከሰቱትና የተካሄዱት ችግሮች በመሉ ተፈጥሮአዊ ያልሆነውን የኮሙኒስትን ርዕዮተ-ዓለም በሚከተሉ ሰዎች የተከሰተ ችግር ነው ብሎ አምኖ መቀበል ነው። ይህ አንድን ነገር በጥቁርና በነጭ መሀከል መለየትና ከዚያም ተነስቶ ትንተና ለመስጠት መሞከር የሃሳብ ግድፈት እንዲኖርና አንድን ችግር ጠለቅ አድርገን እንዳንወያይ ለማድረግ በቅቷል። በመሆኑም ፣ መሰረታዊ የሆኑት የመኖር ትርጉም ጥቄያዎች ፣ የግለሰብን ሚናና የአንድ ህብረተሰብ ትርጉም ፣ እንዲሁም ደግሞ ኢኮኖሚያዊ መሰረታዊ ጥያቄዎችን በሰፊው አንስቶ ለመወያየት ያልተቻለበት ደረጃ ተደርሷል።

ወደድንም ጠላንም ሁላችንም የተወሰነ ዕሴትን እናጸብራቃለን። በአንድ በኩል ከባህል የወረስነው ዕሴት ሲኖረን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከተለያየ ዕውቀትና አመለካከት ጋር የተላመድንና የተጋጨን በመሆናችን ሳንወድ በግድ ይህን ወይንም ያኛውን አመለካከት እንድንይዝ ተገደናል። ይሁንና በኛ መሀከል ያለው የአመለካከት ልዩነት ልክ እንደ አውሮፓው በሰፊ ትንታኔና ዕምነት ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን በአንዳንድ ቦታዎች በጭፍን ዕምነት ላይ የተመረኮዘ ነው ብል ስህተት አይደለም። አንድን ነገር በደንብ ሳይመረምሩ ወደድኩት አልወደድኩትም እንደሚባለው አነጋር ሁኔታ ውስጥ በመግባት ሃሳቦች ተኮላሽተው እንዲቀሩ ሆነዋል። ይህም ተባለ ያ በዕሴትና በርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ ከሚደረገው ትግል ልናመልጥ አንችልም። በሌላ ወገን ግን ወደ ጭፍንነት እንዳናመራ ከፈለግን በርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ ከሚደረግ ውይይት ተላቀን ወደ ንጹህ ምሁራዊ ትግል ብናመራ አገራችን ላጋጠሟት የተወሳሰቡ ችግሮች በቀለሉ መፍትሄ ማግኘት እንችላለን።

ወደ ቲዎሪ አስፈላጊነት ስንመጣ ማንኛውም ነገር ካለቲዎሪ ሊተነተን ወይም ተግባራዊ ሊሆን በፍጹም አይችልም። ያልተማረ ሰው እንኳ ሳያውቀው አንድን ነገር የሚሰራው የተወሰነ ሎጂክናና ቲዎሪን ተከትሎ ነው። ይህንን በቀላል ምሳሌ ማስረዳት ይቻላል። ለምሳሌ የሽሮም ሆነ የስጋ ወጥ የሚሰራ ሰው ሽንኩርት ከትፎ አቁላልቶ ከመብሰሉ በፊት መጀመሪያ ስጋውንም ሆነ ሽሮውን በቀዝቃዛ ውሃ በመበጥበጥ አያማስለውም። ሽንኩርት ከመቁላላቱና ቲማቲም ወይም በርበሬ ጋር ከመዋሃዱ በፊት ከመጀመሪያውኑ በውሃ የሚበጠበጥ ስጋ ወይም ሽሮና በላዩ ላይ ሽንኩርትና በርበሬ እንዲሁም ቅቤ የሚደረገምበት ወጥ ሲበላ ጣዕሙ በፍጹም ሌላ ይሆናል። ይህንን የአሰራር ቅደም ተከተል ለብዙ ነገሮች ማዋል እንችላለን።

ሰፋ ወዳለ የህብረተሰብ ጥያቄ ከመምጣታችን በፊት መጀመሪያ አንድን ነገር በቲዎሪ ለማብላላት መሞከር አለብን። ይህ ደግሞ ለቅንጦት ሳይሆን ፣ በመጀመሪያ የተወሰነ የአሰራር ሎጂክን ለመከተል ሲሆን ፣ በሁለተኛ ደረጃ በቲዎሪ የተጠናና የተብላላ ነገር ከብዙ ስህተቶች ያድነናል። አንድን ነገር በጥንቃቄ እንድንሰራ ይረዳናል። በተለይም የቲዎሪን ትንተና ካስቀደምን ካለምንም ጥርጥር ከርዕዮተ-ዓለም ዝባዝንኬ ሊያድነን ይችላል። ስለሆነም ፣ ከኢኮኖሚ አንስቶ እስከ ፖለቲካና ልዩ ልዩ አንድን ህብረተሰብ የሚመለከቱ ነገሮች በርዕዮተ-ዓለም መነጽር መታየታቸው ቀርቶ በቲዎሪ ቢብላሉና በአርቆ-

አስተዋይነት መነጽር ቢታዩ የተወሳሰቡ ችግሮችን በቀላሉ መረዳት ብቻ ሳይሆን ጥበባዊ ነገሮችን ለመስራት ያለን ኃይል ከፍ ይላል። በኛ አገርም ሆነ በብዙ አፍሪቃ አገሮች ያለው ችግር ከምዕራቡ ዓለም አንድን ነገር በጭፍን መወሰድና ሳይመረምሩ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ከዚህም ስንነሳ ካለብዙ ውጣ ውረድ ባለፉት ሰላሳና አርባ ዐመታት በነፃ ገበያ ስም በብዙ አፍሪቃ አገሮች ተቀባይነትን ያገኘውና ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የቱን ያህል መቀመቅ ውስጥ እንደከተተን መረዳቱ ከባድ አይሆንም። ወደ ጥያቄዎቹ ለምራ።

## የኢኮኖሚና የነፃ ገበያ ጉዳይ

እንደ ዕውነቱ ከሆነ በአሁኑ ወቅት እንደነዚህ ሁለት ጽንሰ-ሃሳቦች አወናባጅ ጉዳይ የለም። በተለይም ኢኮኖሚ እንደ ሳይንስ ከዳበረበት ከ18ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ኢኮኖሚና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ጽንሰ-ሃሳቦችን በሚመለከት ሰፊ ክርክር ተካሂዷል። ዛሬም በሰፊውና በጥልቀት እየተካሄደ ነው። ስለዚህም ሳንወድ በግድ የጽንሰ-ሃሳቡን ምንነት እየመላለስን መጠየቅ ይኖርብናል ማለት ነው።

ኢኮኖሚ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ኦይኮኖሚያ ከሚለው የግሪክ ቋንቋ የመነጨ ሰሆን ፣ ጥንታዊው ትርጉሙ የቤተሰብ(Household) አስተዳደር ማለት ነው። ይህም ማለት የተወሰነ የስራ ክፍፍልና የአስተዳደር ጥበብን የሚመለከት ሲሆን ፣በቤተሰብ ላይ ወይም በግላዊ ክንውን ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለንም የአስተዳደር ስልት ያካተተ ነው።

በዘለማድ ሆኖ ፣ ስለኢኮኖሚ ሲወራ አንዳንዶቹ ሰፋ ካለው ትርጉሙ በመነጠል ፣ ኢኮኖሚክስ ማለት የቁጠባ አያያዝ ዘዴ ነው በማለት ያስቀምጣሉ። ይህ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ትክክል ቢሆንም ፣ ኢኮኖሚ ማለት አንድ ሰውም ሆነ ህብረተሰብ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ጥሬ-ሀብቶችን በማሰብ ኃይሎ አውጥቶ ወደ ሌላ ለጠቀሜታ ወደ ሚውሉ ነገሮች በመለወጥ የሚያካሂደው ጠቅላላው ሰውነታዊና መንፈሳዊ ክንውን ነው። ይህም ማለት ፣ አንድ ሰው ኑሮውን ለማሸነፍ ሲል የሚያደርገው በሱና በተፈጥሮ መሀከል ያለው ግኑኝነትና ፣ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ሰር ማድረግ መቻል ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ይባላል። ይህ ዐይነቱ ክንዋኔ በረቀቀና በቀጥታ በሚታይ መልክ የሚካሄድ በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል ያለ ግንኙነት ብቻ አይደለም። ማንኛውም ግለሰብ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ጥሬ-ሀበቶችን አውጥቶ ለመጠቀም የግዴታ ከአንድ መሳሪያ ጋር የተጣመረ ኃይል(Energy) ያስፈልገዋል። በመሆኑም የምርት ክንውን ዘዴና ፣ ብቃትና የምርት ጥራት በአምራቹ ዕውቀትና በመሳሪያው ውስጥ በተከማቸ ኃይልም ይወሰናል ማለት ነው። በዚህም መሰረት የአመራረት ዘዴ ፣ የምርት ዐይነትና የፍጆታ አጠቃቀም በጊዜ ደረጃ ይለያዩ እንጂ አንድ ላይ ተጣምረው የሚሄዱ ናቸው። ባጭሩ ፣ ማንኛውም የምርት እንቅስቃሴ ባዮሎጂካል ፣ ፊይዚካልና ኬሚካላዊ ክንውን ነው። ወደድንም ጠላንም ማኝኛውም ምርት በዚህ መልክ ቀስ በቀስ ከታች ወደ ላይ የሚካሄድ የአመራረት ስልት ነው።

በኛ አገር የዘልማድ አነጋገር ኢኮኖሚ በጣም በተቆጠበ መልኩ መታየቱ ብቻ ሳይሆን ፣ ማንኛውም የኢኮኖሚ ክንውን ከስራ ክፍፍል ጋር የተያያዘ እንዳለሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው። ብዙ ጊዜ በስህተት የስራ-ክፍፍል አባት አዳም ስሚዝ ነው ተብሎ ይነገራል። የስራ ክፍፍል አስፈላጊነትና ምንነት በግሪክ ስልጣኔ ዘመን የታወቀና ፣ አንድ ህብረተሰብም ካለስራ ክፍፍል መኖር እንደማይችል የታመነበት ነው። ስለዚህም ፣ ማንኛውም ህብረተሰብ በተቀነባበረ የስራ ክፍፍል ብቻ ነው ህብረተሰብአዊ ግኑኝነትን ማጠንከርና ራሱን መግለጽ የሚችለው። ይህም ማለት ፣ ማምረት ፣ የንግድ ልውውጥ ማድረግና የሀብት ክፍፍል እንደ ኢኮኖሚና ህብረተሰብአዊ ዕድገት ደረጃዎች አንድ ላይ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው። የስራ ክፍፍል አስፈላጊነት ግልጽ የሆነበት ምክንያት ፣ ግለሰብም ሆነ በቤተሰብ የተደራጀ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ብቻውን ማምረት ስለማይችል የግዴታ በህብረተሰብአዊ የስራ-ክፍፍል አማካይነት ፍላጎቱን ማሟላት ይችላል ከሚለው መሰረታዊ ሃሳብ በመነሳት ነው።

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የስራ ክፍፍል መኖር በጊዜና በቦታ የሚወሰን ነው። አንድን ምርት ለማምረት የተወሰነ የክንውን ጊዜ ያሰፈልጋል። ምርቱም ከማምረቻው ቦታ ወደ ተጠቃሚው ለመድረስ የተወሰነ ርቀትን መጓዝ አለበት። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በፍጥነት ለመድረስ ባለው የግኑኝነት መስመርና ዘዴ ይወሰናል። ይህ ጉዳይ የጊዜን ወሳኝነት ሲያመለክት ፣ ለንግድ ልውውጥ የግዴታ መለዋዋጫ ቦታ ወይም ገበያ ያሰፈልፈጋል።

በታሪክ ሂደት ባደገ የገበያ አማካይነት ብቻ ነው የዕቃዎች የርስ በርስ ልውውጥ ፣ ወይም ደግሞ ዕቃዎች በገንዘብ ሊለወጡ የሚችሉት። ስለዚህም የኢኮኖሚ ክንዋኔ በአንድ ቃል ሊተረጎም የሚችል ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገሮችን ያጣመረ ነው። ኢኮኖሚ ማለት ንግድና የፍጆታ አጠቃቀም ብቻ አይደለም። ኢኮኖሚያዊ ክንውን ማለት ፣ማቴሪያላዊ ፣መንፈሳዊና ጥበባዊ ነው። ጥበባዊ የሚያሰኘው ፣ ማንኛውም ምርት ቆንጆና ጥራት ባለው መልክ መመረቱ ብቻ ሳይሆን ፣ ምርቱ የሚሸጥበት ቦታ ራሱ ጥበባዊ ወይም የሚያምር መሆን ስላለበት ነው። ይህ ደግሞ የባህል ዕድገት ነፀብራቅ ነው። የነፃ-ገበያ እንደ ርዕዮተ-ዓለም ባሸናፊነት ከወጣበት ከ18ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የተያዘው ጉድ በነፃ ገበያ ሽፋን ስር የምርት ክንውን ጥራት እንዳይኖረው ማድረግ ብቻ ሳይሆን ፣ የሰውን ልጅ መንፈስ በነፃ ገበያ ሎጂክ ክልል ውስጥ በማሽከርከር ማንነቱን ስቶ የተዝረከረከ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ ነው። ኢኮኖሚ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ መሰረታዊ ከሆኑት ባይሎጂካል ፣ፊይዚካልና ኬሚካላዊ ክንውኖች ተነጥሎ በመታየቱና ፣ በተለይም ደግሞ ኢኮኖሚና የአንድ ህብረተሰብ ዕድገት ተነጥለው በመታየታቸው ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ህብረተሰቦች ብዙም ሳያወጡ ሳያወርዱ የወሰዱትና ተግባራዊ ያደረጉት ጽንሰ-ሃሳብ መቀመቅ ውስጥ ሊከታቸው በቃ። ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔን በሰአትና በቦታ ማየትና ከዚህም አንፃር ማስላትና መተንተን ሲገባቸው በተወሰነና በጠባብ መሳሪያ ብቻ በመመራት ህብረተሰብአችን ተዝረክርኮ እንዲኖር ተገደደ።

የነፃ ገበያ የሚለው አሳሳችና ርዕዮተ-ዓለማዊ መፈክር ዋናው ዐላማ አንድን አገር ወይም ህብረተሰብ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት መድረክ አድርጎ ማየቱ ነው። በዚህም መሰረት የማንኛውም ህብረተሰብ ወይም ግለሰብ ዋናው ዓላማ ንግድ ማካሄድና ትርፍ ማትረፍ እንጂ ፣ አንድን ህብረተሰብ ጥበባዊ በሆነ መልክ ረጋ ባለ ሁኔታ መገንባት አይደለም። የማንኛውም ግለሰብ አስተሳሰብና መንፈስ በዚህ በሚያንቀጀቅጅና ስግብግብ በሚያደርግ እንዲሁም ደግሞ ህብረተሰብን በሚያዝረከርክ የነፃ ገበያ ሎጂክ ውስጥ ማሽከርከር ነው። መገበያየትና ገበያ መኖር የግዴታ ታሪካዊና የህብረተሰብ ዕድገት ውጤቶች ቢሆኑም ፣ ነፃ የሚለው መፈክር ብዙ ሰዎችንና ህብረተሰቦችን በማሳሳት በየአገሮቻቸው ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን በዝግታና በስርዐት እያወጡና እየለወጡ እንዳይጠቀሙ አግዷቸዋል። ስለዚህም ነፃ ገበያ የሚለው መፈክር ፣ ወደ ስግብግብነት የሚያመራ ብቻ ሳይሆን ፣ አንድን ህብረተሰብ የመራኮቻ መድረክ የሚያደርግና በተለያዩ ህብረተሰቦችም መሀከል ጦርነትን የሚጋብዝ መፈክር ነው።

ስለሆነም ፣ በብዙ የአፍሪቃ አገሮችና በአገራችን የተወሰደውና ተግባራዊ የሆነው የነፃ ገበያ መፈክር አደገኛነቱ ፣ በዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍልና በስትራቴጂክ የጥሬ-ሀብቶች አስፈላጊነት መሰረት አገሮችን ህብረተሰብአዊ ዕሴቶች መገንቢያና ህዝቦችም ህልማቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት መድረክ መሆኑ ቀርቶ ወደ ጦር አውድማነት በመለወጥ ህዝቦችን እያተራመሰ ነው። በተለይም የቻይና ኢኮኖሚያዊና ሚሊታራዊ ኃያልነት እየገፋ በመጣበት ወቅት ፣ በኔቶ የሚመራው ወራሪ ኃይል በአዳዲስ መሳሪዎች እየታገዘ አገሮችን በአንድ በኩል በነፃ ንግድ ርዕዮተ-ዓለም ወጥሮ ይዞአቸዋል ፤ በሌላ ወገን ደግሞ የጦር መፋለሚያ መድረክ ወደ ማድረግ እያመራ ነው። በመሆኑም የነፃ ገበያ ከውስጥ እየቦረቦረንና ህብረተሰብአችንን በማዝረክረክ ከውጭ ደግሞ እንድንወረር የሚጋብዝ አደገኛ ርዕዮተ-ዓለም ነው ማለት ነው።

እነ አዳም ስሚዝና ሪካርዶ መርካንታሊዝምን በመቃወም በአገሮች መሀከል የነፃ ገበያ መኖር ዕድገትን ያመጣል ብለው ሲያስተምሩ ፣ የነፃ ገበያ ከሁለት መቶ ዐመት በኋላ የሚያስከትለውን ጠንቅ አልታያቸውም ነበር። የዓለም ማህበረሰብም እንደዚህ እየተወሳሰበና የሰው ልጅም ዕድል በጥቂት መረን በለቀቁ ኃይሎች ፍዳውን ያያል ብለው አልገመቱም ነበር። ሁሉም ነገር ካለፍጥጫ በሰላምና በመግባባት በእኩልነት ደረጃ የሚካሄድ መስሎአቸው ነበር። ግሎባል ካፒታሊዝም በዚህ መልክ ተደራጅቶ የዓለምን ጥሬ-ሀብትና የንግድ እንቅስቃሴ መወሰኑ ብቻ ሳይሆን ፣ እንደ ዓለም ባንክ ፣ የዓለም የገንዘብ ፈንድና የዓለም የንግድ ድርጅት የጥቂት አገሮች መሳሪያ በመሆን እንደዚህ ዐይነት ዓለም አቀፋዊ የህብረተሰብ መመሰቃቀልና ጦርነቶች ይከሰታሉ ብለው በፍጹም አልገመቱም ነበር። በማርክሲዝም ዳስ ካፒታል ቲዎሪ የታነፁት እነ ሮዛ ሉክሰምበርግ ግን ጦርነት የዚህ ዐይነቱ ልቅ ዓለም አቀፋዊ ካፒታሊዝም ሂደትና በሞኖፖል ደረጃ መዋቀር ክስተቶች መሆኖቸውን በሚገባ ጠቁመዋል። በተጨማሪም ፣ የምርት ክንውን ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ሲይዝ እዚህና እዚያ የሚተከሉት ተቀጣይ ኢንዱስትሪዎች የተስተካከለ ዕድገትን ለማምጣት እንደማይችሉ አስተምረዋል። ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነቱ የግሎባል ካፒታሊዝም እንቅስቃሴ በርካሽ ዋጋ አምርቶ ብዙ ትርፍ ለማትረፍ ስለሆነ የአንድ አገር የውስጥ ገበያ አደገ አላአደገ ደንታው አይደለም። የሚተከሉት ኢንዱስሪዎች ሀብት አባካኝ በመሆን ወደ ውስጥ በተለያዩ መስኮች ብቻ ሳይሆን ፣ በገጠርና በከተማ መሀከል ያለውን ዕድገት የሚያዛባ ይሆናል። ዛሬ በተለይም በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ያለው ችግር ይህ ነው። የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች

በተወሰኑ ቦታዎች መካሄድ ከየቦታው የሰውን ኃይል እንዲመጥ አድርጓል። በከተማዎች በቀላሉ ስራ ማግኘት የማይችል የህብረተሰብ ክፍል ተፈጥሯል። በተጨማሪም ፣ የጥሬ-ሀብቶችም መበዝበዝና ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚራገፈው ቆሻሻ ምርት የዚህ ልቅ ካፒታሊዝም ዕድገትና ገበያዎችን የመቆጣጠር ውጤቶች ናቸው። ይህም ማለት ብዙ የሚያከራክሩና ፣ በብዙ ኢትዮጵያኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ የማይችሉ ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች ቢኖሩም ፣ ያለው ሀቅ ግን የዓለም ገበያ ከፍተኛ ፍልሚያ የሚደረግበት የፍጥጫ መድረክ ነው። ብዙ ህጋዊ ነገሮች ቢደረደሩምና ሁሉም አገሮች ተቀብለነዋል ቢሉምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ቢመስልም ፣ በስተጀርባው የሚካሄደው ትግል ግን ደካማ አገሮችን ተበዝባዥና ለህብረተሰብ የማያስፈልጉ ቆሻሻ የፍጆታ ዕቃዎች ማራገፊያ መድረክ ማድረግ ነው። የነፃ ገበያን ውስጣዊ ክንዋኔ ከዚህ ውጭ ማየት ስህተት ነው ማለት ነው። አንድንም ህብረተሰብ በነፃ ንግድ አማካይነት መለወጥ ይቻላል የሚለው መፈክር ሊሰራ የማይቻለው ከግሎባል ካፒታሊዝም ውስጣዊ ሎጂክ በመነሳት ብቻ ሳይሆን ፣ በየአገሮች የተተከሉት የአገዛዝ መዋቅሮችና ከውጭው ዓለም ጋር በሺህ ድሮች መተሳሰር ወደ ውስጥ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት ለመፍጠር ስለማያመቹ ነው።

## በነፃ ገበያና በካፒታሊዝም መሀከል ያለው ልዩነት

ብዙ ጊዜ ስለ ነፃ ገበያ ሲወራ ሁሉም ነገር በጠያቂና በአቅራቢ የሚደነገግበት መድረክ እንደሆነ ነው። ሁሉም እንደ አስተዋጽኦው የየራሱን ድርሻ የሚያገኝበት ነፃ መድረክ ነው። በደሞዝ ተቀጥሮ የሚሰራው እንደ ችሎታውና እንደ አስተዋጽኦው ሲያገኝ ፣ መሬትን የሚያከራይና ካፒታል ኑሮት ለመዋዕለ-ነዋይ የሚያውለው በየበኩላቸው እንደ የአስተዋጽኦአቸው ድርሻ ይኖራቸዋል። በኒዎ-ክላሲካል ኢኮኖሚስቶች ዕምነት ሁሉም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሳተፉት ኃይሎች የሚያገኙት ድርሻ የምርታማቸው ውጤት ነው። የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ፖለቲካል ኢኮኖሚክስ የሚለውን አነጋገር ሲቃወሙ ፣ የሚነሱበት የትንተና መነሻ የምርትን ሁኔታና መልሶ መላልሶ ማምረትን በመቃወም ነው። የጥሬ ሀብቶች እንደልብ ስለማይገኙ በገበያ ወስጥ በሚደረገው ልውውጥ አማካይነት የጥሬ ሀብቶች በጠያቂና በአቅራቢ ህግ መሰረት ተገቢ ቦታቸውን ያገኛሉ። በገበያ ላይ የሚሳተፉት ኃይሎች አርቀው የሚያስቡ ስለሆነ አስፈላጊውን ኢንፎርሜሽን በመሰብሰብ ከፍተኛ ጥቅም ለማግኘት ይችላሉ። ስለሆነም በገበያ ውስጥ የሚሳተፉት ኃይሎች ዋና ዓላማ የራስን ጥቅም ማሳደድ ብቻ ነው።

በዚህ መሰረት ፣ እነዚህ ሶስት ኃይሎች በጊዜና በቦታ የሚወሰኑ ሳይሆን ወይም ደግሞ በህብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ከረዢም ጊዜ ክንውን በኋላ የሚከሰቱ ሳይሆኑ እንደ ቋሚ ሆነው(given) የሚወሰዱ ናቸው። ውስጣዊ-ኃይል የሌለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ነው ማለት ነው። በውድድር አማካይነት የሚፈጠር የቴክኖሎጂ ምጥቀትና የኢንዱስትሪዎች ስብሰብና(Concentration of Capital) እንዲሁም ደግሞ ሀብት ከአንድ ዘርፍ ወደ ሌላ ቦታ መሸጋሸግ አይኖርም። ስለዚህም የገበያ ኢኮኖሚ የረዢም ጊዜ የህብረተሰብአዊ ክንውንና ምሁራዊ የትግል ውጤት ሳይሆን ያለና የነበረ ነው። የኃይል አሰላለፍ ትግልም ውጤት አይደለም። ስለዚህም ፣ ህብረተሰብአዊ ሀብትም የሚፈጠረው አዳም ስሚዝ ወይም ጠቅላለው የክላሲካል ኢኮኖሚቶች እንደሚሰተምሩን ፣ በሰራተኛው የስራ ውጤት ሳይሆን ሁሉም ኃይሎች በሚያደርጉት አስተዋጽኦ ነው። በዚህም መሰረት የኒዎ-ክላሲካል ወይም ዛሬ ኒዎ-ሊበራል ተብሎ የሚታወቀው የኢኮኖሚ ዘርፍ ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት በሰራተኛው መፈጠሩን አይቀበልም። የዕቃዎች ዋጋም በሰራተኛው አስተዋጽኦ የሚደነገግ ሳይሆን ፣ በአቅራቢና በጠያቂ መሀከል የሚወሰን ነው። በሌላ አነጋገር ፣ ለሰራተኛው የሚወጣው ቀጥተኛ ወጪና ለማሺኖች የሚወጣውና በየአመቱ የሚቀንሰው የማሺኖች ዋጋ ውጤት አይደለም የየዕቃዎች ዋጋ መተመኛ። የተቆጠበው የጥሬ-ሀብት(Scarce resources) በተለያዩ መስኮች እንደየ አጠቃቀማቸው መሰማራትና ተግባራዊ መሆን እንዲሁም በጠያቂና በአቅራቢ አማካይነት ነው የአንድ ዕቃ ዋጋ የሚወሰነው።

በሌላ ወገን ግን የአዳም ስሚዝ የገበያ ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ ከታች ወደ ላይ ያደገ ሲሆን ፣ በተወሰነ የስነ-ምግባር ክልል ውስጥ መካሄድ ያለበት ነው። ይሁንና ግለሰብአዊ ድርጊት በረቀቀው ኃይሉ የቴክኖሎጂ ምጥቀትን ያሰከትላል። በዚህም ምክንያት በኢኮኖሚው ውስጥ በተለያዩ መስኮች ሚዛናዊ ሁኔታ ይፈጠራል። የስራ ክፍፍል መኖር

ለህበረተሰብአዊ ሀብት መፈጠር አመቺ ሁኔታን ሲፈጥር ፣ ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብትን(Social Wealth) ሊፈጥር የሚችለው የሰራተኛው ጉልበት ብቻ ነው። ወይም በትክክለኛ አነጋገር *Labour is the source of value* በመሆኑም በተግባር ላይ የሚሰማራው ካፒታል የረዥም ጊዜ የስራ ውጤት ወይም ደግሞ የተከማቸ የሰራ ውጤት ሀብት ነው። ይሁንና ፣ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶችም ሆነ የእነ አዳም ስሚዝ አመለካከት በኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ሀብት መሽጋሸግ የተነሳ ህብረተሰብአዊ ግጭት ይኖራል ብለው ከግምት ውስጥ አያስገቡም። በመሆኑም ሀብትን በሚቆጣጠሩና በሰራተኛው መሀከል ያለው ግኑኝነት ተፈጥሮአዊ ክንውን ነው።

የካፒታሊዝም ትርጉም ዛሬ በሁሉም ዘንድ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ ተቀባይነት ቢያገኝም ፣ በአንድ በኩል የታሪክና የህብረተሰብ ዕድገት ውጤት ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የተወሰነ ህብረተሰብአዊ ግኑኝነትን የሚያመለከት ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ነው። ህብረተሰብአዊ ግኑኝነት የሚለው በኢኮኖሚው ውስጥ በሚሳተፉ ኃይሎች መሀከል እኩልነት እንደሌለ ያመለክታል። ስለሆነም ፣ የወዝ አደሩ ጉልበት ልክ እንደ ማንኛውም ዕቃ በገበያ ላይ የሚሸጥና የሚለወጥ ሲሆን ፣ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ ዕውነተኛ ዋጋን(Value) ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን ለራሱ ኑሮ ከሚያሰፈልገው ሰዓት በላይ በመስራት የጠቅላላውን የካፒታሊዝምን ዕድገት ወሳኝ ነው። ይህ ትርፍ የስራ ሰዓት(Surplus Value) የትርፍ ምንጭ ብቻ ሳይሆን  የወለድና የመሬት ኪራይ ምንጭም በመሆን በተለያዩ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሳተፉትን ኃይሎች ሀብትና ገቢ ይወስናል። መልሶ መላልሶ ኢንቬስት ማድረግም ሊወሰን የሚችለውም በወዝ አደሩ ተጨማሪ የሰራ ሰዓት ውጤት ነው። በማርክስ አባባል ፣ ካፒታሊዝም ከተራ ሸቀጣ ሸቀጥ ወደ ተወሳሰበ የአመራረት ዘዴ በመሸጋገር የኢንዱስትሪ ሀብት በአግዳሚም(Horizontal) ሆነ ከታች ወደ ላይ(Vertical) በመሸጋሸግ  ሀብት በተወሰነ የኢንዱስትሪ ዘርፍ በመከማቸት የግዴታ ከባንክ ካፒታል ጋር እየተቆላለፈ ይመጣል። ስለሆነም ፣ ይህ ዐይነቱ ካፒታሊዝም ትናንሾችን በመጨፈላለቅ ፣ ወድድሩ በትናንሽ ካፒታሊሰቶች መሀከል መሆኑ ቀርቶ ጥቂት ገበያውን በሚቆጣጠሩ ሞኖፖሊሰቶች መሀከል ይሆናል ይላል። ይህ የውስጠ-ኃይል ክንውን(dynamic process) የግዴታ በየጊዜው ለሚከሰት የኢኮኖሚው ቀውስ ምክንያት ይሆናል። ምክንያቱም ፣ የቴክኖሎጂዎች ምጥቀትና ክምችት የሰራተኛውን መጠን እንዲቀንስ ሲያደርግ ፣ በዚያውም መጠን የሚበዘበዘው የሰው ኃይል ይቀንሳል። ይህ ሁኔታ ቋሚውን ካፒታል(fixed capital) ስለሚያሳድገው ፣ በቋሚው ካፒታልና በሰራተኛው(Variable Capital) መሀከል ያለው መዛባት ከፍ እያለ ይሄዳል። በዚያው መጠንም የትርፉ መጠን (The rate of profit) ይቀንሳል ይላል። የትርፉ መጠንም ሲቀንስ ካፒታሊስቶች ኢንቬስት ከማድረግ ይቆጠባሉ ፤ ወይም ሌላ ዐይነት ውድድር በመፍጠር ወደ ተወሳሰበና ጥልቀት(Capital deepinig or rationalization) ወዳለው ቴኮኖሎጂ በማምራት የጠቅላላውን የምርት ክንውን ዋጋ በመቀነስ ትርፍ የሚያካብቱ ስለሚመስላቸው የሰራተኛውን የመደራደር ኃይል ይቀንሳሉ። ይህ ዐይነቱ ቴክኖሎጂዊ ምጥቀትና የሀብት ክምችት ወደ አንድ አቅጣጫ ሲያዘነብል ፣ የኢንዱስትሪዎች በባንክ ካፒታል ላይ መመካት ከፍ እያለ ይመጣል። ይህም ሁኔታ ለህብረተሰብአዊ ግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል ይላል። የትርፍ መቀነስ ፣ በቀላሉ ገዢ የማያገኝ ምርት መከማቸትና የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል መቀነስ ለካፒታሊዝም ቀውስ ዐይነተኛ ምክንያቶች ሲሁኑ ፣ ይህን ዐይነቱን ቀውስ ጋብ ማድረግ የሚቻለው በተከታታይ ከባንክ በሚገኝ ብድርና ይህንን ለዕቃዎች ግዢ በማዋል ነው። በሌላ አነጋገር ፣ ብድር ለካፒታሊዝም ዕድገትና የዕቃዎች መሽከርክር ወሳኝ ሚናን ይጫወታል ማለት ነው።።

በዚህም ምክንያት የፊናንስ ካፒታል ከፍተኛ ቦታን በመያዝ ፣ የገንዘብ ዕድገት ከዕቃ ባህርይው(Commodity Character) በመላቀቅ የብድር ገንዘብ ወይም ክሬዴት ገንዘብና በልዩ ልዩ መልክ የሚከሰቱ የገዘብ ዐይነቶች ለስርዐቱ ምጥቀትና ስፋት ሊሰጡት ቻሉ። የዕቃዎችም መሽከርከር በኢኮኖሚው ውስጥ በሚሽከረከረውና በክሬዲት መልክ በሚገኘው ገንዘብ አማካይነት ነው ሊወሰን የሚችለው። በዚህም ምክንያት ገንዘብ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ልዩ ህብረተሰብአዊ ኃይል በመሆን ዛሬንና ነገን የሚያገናኝ  መሳሪያ ነው። ባጭሩ ፣ የካፒታሊሰት ኢኮኖሚ በጣም ፈጣን የሆነውን ያህል በሰዎች ላይ የሚኖረው ጭነት  ከባድ ከመሆኑ የተነሳ በቀጥታ ከሚታይ ህብረተሰብአዊ ግጭት በማለፍ ወደ ህሊና ቀውስ እንዲያመራ ያደርጋል። የሰዎች የማሰብ ኃይል ከቴክኖሎጂያዊ ምጥቀት ጋር ሊጓዝ አይችልም ማለት ነው።

በኒዎ-ሊበራልና በማርክሲስቶች መሀከል የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ዕድገትና ውስጠ-ኃይል በሚመለከት ይህን የመሰለ ልዩነት ሲኖር ፣ ሁለቱም ምሁራዊ እንቅስቃሴዎች ስለ አንድ ነገር እያወሩ ፣ የአተናተን ዘዴያቸው ግን በፍጹም ይለያል። በኒዎ-ሊበራል

ኢኮኖሚስቶች ዕምነት ፣ የገበያ ኢኮኖሚ እድገት በሰዎች ባህርይ የሚወሰን ሲሆን ባህርያቸውን በልዩ ልዩ ዘዴ መቀየር(manipulate) ይቻላል። ስለሆነም የትንተናው ዘዴ ከባህርያቸውና ከፍጆታ አጠቃቀማቸው ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም በስርዐቱ ውስጥ የሚከሰተው ቀውስ ከውስጥ በሚፈጠር የውስጠ-ኃይል ክንዋኔ ሳይሆን ፣ የውጭው ኃይል በሚፈጥረው ያልተጠበቀ ምክንያት ነው።

ኒዎ-ሊበራሊዝም የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ከካፒታሊስት ዕድገት ጋር አያይዞ መመለስ ይቻላል። በመጀመሪያ ግን ቀደም ብለው ካለኒዎ-ሊበራሊዝም መፍትሄ ሊኖር አይችልም ብለው ሽንጣቸውን ገትረው የሚታገሉ ኃይሎች ያራግቡ የነበረውን እየወነጀሉና የግዴታ ኢኮኖሚው ቁጥጥርና አርቆ-አሳቢነት ያስፈልገዋል እያሉ እየወተወቱ ነው። ባጭሩ ግን ኒዎ-ሊበራሊዝም የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ሲቃወም ፣ ኢኮኖሚው በውስጣዊ ኃይሉ ራሱን በራሱ የሚያሰተካክል ነው። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሳተፉ ኃሎች በሙሉ የታሪክ ክስተት ሳይሆኑ የተሰጡ እንደመሆናቸው መጠን ፣ የነዚህ ተመጥኖና ሳይመጠን መኖር ጠቅላላውን የጥሬ-ሀብት በተለያዩ ዘርፎች ዘንድ መከፋፈልንና ለምርት ክንውን መዋልን ይወስናል ይላል። በኒዎ-ሊበራሊስቶች ዕምነት ማንኛውም የሞነተሪ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። የገንዙቡም መጠንና እንቅስቃሴ በወለድና በፊስካል ፖሊሲ አማካይነት መስተካከል አለበት። የገበያ ወለድ(Interest rate) ከፍ በሚልበት ጊዜ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሽከረከረውም ገንዘብ ዝግ ይላል ወይም ይቀንሳል። በዚህም ምክንያት በዕቃዎች ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ምክንያቱም በኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ዕምነት የገንዘብ መጠን ነው የዕቃዎችን ዋጋ ሊወስን የሚችለው። ይሁንና ግን በካፒታሊዝም ውስጠ-ኃይል የተነሳ በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚሽከረከረው ገንዘብ በባንክ አማካይነት ብቻ የሚወሰን መሆኑ ቀርቶ እንደ ኢንሹራንሰ(Financial intermidiaries) በመሳሰሉትም ኢንስቲቱሽኖች የሚወሰን ነው። ከዚህ በተረፈ ከአንድ ዐመት በፊት የፊናንስ ቀውሱ ከመከሰቱ በፊት የነበረው ዕምነት ማንኛውም በመንግስት የሚካሄድ የፊስካል ፖሊሲ ዞሮ ዞሮ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚሽከረከረውን የገንዘብ መጠን ያበዛዋል ፤ የዋጋ ግሽበትም ያስከትላል ብለው የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ያምኑ ነበር። በዚህም ምክንያት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሽከረከረው የገንዘብ ብዛት የተወሰነ መጠንን ይዞ መጓዝ ሲኖርበት በኢኮኖሚው ውስጥ በሚመረተው ምርትና በጠቅላላው የገንዘብ መጠን ሚዛናዊ ሁኔታ ይፈጠራል ይላሉ። የካፒታሊዝም ዲይናሚዝም ግን በዚህ መልክ የሚሰራ አይደለም። የውስጠ-ኃይሉ መፍጠንና ማደግ የግዴታ ከባንክ በተለያየ መልክ ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈሰውና ከባንክ ውጭ ባሉ ኢንሰቲቱሽኖች አማካይነት ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈሰው ገንዘብ ፣ የገንዘብን ከዕቃዎች ምርት በላይ መሽከርከርን ያስከትላል። ይህ ማለት ግን ግሽበት ይከሰታል ማለት አይደለም። ይህ ቢሆን ኑሮ ከአንድ ዐመት ጀምሮ ኢኮኖሚውን ከገባበት ቀውስ ለማዳን የተወሰዱት የወለድ ቅነሳና የፊስካል ፖሊሲዎች ከፍተኛ ግሽበትን ባስከተሉ ነበር። በብዙ የኢንዱስትሪ አገሮች እንደምናየው ዕቃዎች በእጥፍ በመቀነስ እየተሸጡ እንደሆን ነው። በሌላ ወገን ግን የገንዘብ ካፒታል እየተስፋፋ ሲመጣ ፣ ከተጨባጭ መዋዕለ-ነዋይ በመለቀቅ ራሱን የቻለ ልዩ የፊናንስ መስክ በመፍጠር ለካፒታሊዝም ልዩ ዐይነት የቀውስ ምክንያት ሊፈጥር ችሏል። በሌላ አነጋገር ፣ ለዛሬው ቀውስ ዋናው ተጠያቂ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ሳይሆኑ ፣ ራሱ የካፒታሊዝም ውስጠ-ኃይል ለቀውሱ ዋና ምክንያት ነው። በተጨማሪም የሀብት በተወሰነ ቦታ መከማቸትና የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል መዳከምና በብድር ላይ መመካት ለኢኮኖሚው ቀውስ ዐይነተኛ ምክንያት ሆኗል። የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶችን ተጠያቂ የሚያደርጋቸው የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ይዘትና ህግ በተሳሳተ መልክ ስለሚያሰተምሩና ካፒታሊዝም ካልምንም መንግስታዊ ጣልቃ ገብነት ሊያድግና ሊስፋፋ ይችላል ብለው በመስበክ ነው። ስለሆነም ፣ ያለውን ተጨባጭ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማፈን ከተጨባጩ ሁኔታ በመራቅና አዳዲስ የሀብት መምጠጫ ሞዴሎች በመፍጠር የሀብት ሽግሽግ ከታች ወደ ላይ እንዲፈስ በማድረግ የቀውሱን ሂደት አፋጥነውታል። በተለይም ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ የተከሰተውን የፊናንስ ካፒታል ከተጨባጩ ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ እየተነጠለ መምጣትና ራሱን የቻለ ዘርፍ ሆኖ ማደግና መስፋፋት ከካፒታሊዝም ዲይናሚዝም ጋር ሊታይ የሚችል ትክክለኛ አተናተን ነው። ስለዚህም ሰለ ኒዎ-ሊበራሊዝም ተጠያቂነት ሲወራ ከጠቅላላው የካፒታሊዝም የውስጠ-ኃይል ነጥሎ ማየት በፍጹም ስህተት ነው።

# ካፒታሊዝም ሊታለፍ የማይችለው ስርዓት ?

ስለካፒታሊዝም እንደ ስርዓት አስፈላጊነት በምናወራበት ወይም በምንጽፍበት ጊዜ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት እንጂ በሌላ አገር እንደዚህ ዐይነት ስርዓት ተግባራዊ ስለሆነ እኛም የግዴታ መውሰድ አለብን ከሚለው በመነሳት አይደለም። እንደዚህ ብለን ከመስበካችን በፊት ባለፈው ጽሁፌ ላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት የአገራችንን ማቴሪያላዊ ሁኔታና የሰውን አስተሳሰብ እንዲሁም ደግሞ ውስጠ-ኃይሉ ጠንካራ የሆነ የህብረተሰብ ኃይል መኖርና አለመኖርን መመርመር ያስፈልጋል።

በኛ አገር የተፈጸመው ትልቁ ወንጀል ካፒታሊዝምን ሁለንታዊ የሆነ ስርዓትና የረዥም ጊዜ የህብረተሰብና የታሪክ ሂደት ውጤት አድርጎ ለመቀበል አለመቻል ነው። በብዙ ሺህ መጽሀፎች እንደተረጋገጠው ዛሬ በምዕራቡ ዓለም የበላይነትን የተቀዳጀው የካፒታሊዝም ስርዓት ልዩና በአውሮፓ ብቻ የታየ ነው። በሌሎች ህብረተሰቦች ውስጥ በዚህ መልክ የተካሄደ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በፍጹም አልታየም። የታሪክ አጋጣሚዎችና በውስጥ የሰፈነው ስርዓት ከውጭ በመጣ የዕቃና የባህል ልውውጥ ግጭት የግዴታ ከውስጥ የአመራረትንና የአስተሳሰብን ለውጥ አስከትሏል። በብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች የተካሄደው ፣ በተለይም ገበሬውን ከመሬቱ ማፈናቀልና ለኢንዱስትሪ የሚሆን ጥሬ ሀብት ማስፋፋት የግዴታ ለካፒታሊዝም ዕድገት ዐይነተኛ ምክንያት ሆኗል። ወደ ውስጥ የተፈጠረው የህብረተሰብ አወቃቀርና ሊቀጠር የተዘጋጀ ኃይል መኖርና ራሱንም መሸጥ የተገደደው ሰራተኛ በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ወደ ውጭ ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች አስገድዶ ጥሬ-ሀብት አምራች ማድረግ ለምዕራቡ ካፒታሊዝም ዕድገት በቂ ምክንት ሆኗል ማለት ይቻላል። የግል ሀብት መኖር ለካፒታሊዝም ማደግ እንድ አንድ ምክንያት ሊወሰድ ቢችልም ፣ ዋናው ምክንያት ግን የዚህ ኢንስቲቱሽናዊ መሆንና የሀብት ክምችት ምንጭ የሆነው የሰራተኛው ህብረተሰብ ሰጥ-ለጥ ብሎ መስራት ለአጠቃላይ የካፒታሊስት ክምችት መንገድ ከፍቷል ማለት ይቻላል። እጅግ የተወሳሰበውን የካፒታሊዝምን ሂደትና እዚህ አጭር ጽሁፍ ላይ ማቅረብ የማይቻለውን ሳይተነትኑ የግዴታ ካፒታሊዝም ያስፈልገናል እያሉ መስበክ ትልቅ ወንጀል ነው። በሌላ ወገን ግን ይህንን እየሰበኩ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የተካሄዱትና በገበያ ስም ተግባራዊ የሆኑትን ፖሊሲዎች ለተመለከተ በካፒታሊዝም ስም ትልቅ ወንጀል እንደተሰራ ማየት ይቻላል።

ይህ ከላይ የተተነተነው መሰረታዊው የካፒታሊስት ቅድመ-ሁኔታ ሲሆን ፣ በምዕራብ አውሮፓ በዕውቅ የተወሰዱት ወደ ውስጥ ፣ የውስጥ ገበያን ማዳበርና ማስፋፋት መሳሪያዎች ለካፒታሊዝም ዕድገት ዕምርታን ሰጥተውታል። በመጀመሪያ ፣ በማደግ ላይ ይገኙ የነበሩትን ኢንዱስትሪዎች ከውጭ በሚመጡ ተመሳሳይ ምርቶች እንዳይመቱ በከፍተኛ የግምሩክ ቀረጥ አማካይነት መከላከል ተገቢ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት በጥራት በማሳደግ ወደ ውስጥ የወርቅን ክምችት ከፍ ማድረግ ነበር። በጊዜው ወርቅ የሀብት ክምችት መሳሪያ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሽከረከረው ገንዘብ ወደ ውጭ በሚወጣና ወደ ውስጥ በሚገባው የወርቅ መጠን እየተደገፈ የሚወሰንና የሚሽከረከር ነበር። ሶስተኛ ፣ የነቁ ኃይሎችን መርዳት ዋናው የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሳሪያ ነበር። በዚህም አማካይነት አዲስ ኢኮኖሚያዊ ኃይል ብቅ ሊልና የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ችሏል። በእነዚህ ዕውቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አማካይነት ብቻ ጠቅላላው የኢኮኖሚ አወቃቀር ከተተበተበት ሰንሰለት መፈታትና ለአዳዲስ ኃይሎችና ለፈጠራ በር እየከፈተ ሊመጣ ችሏል። ይህ ቅድመ-ሁኔታ ባይኖር ኑሮ የእነ አዳም ስሚዝ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ተግባራዊ ሊሆን በፍጹም አይችልም ነበር። ስለዚህ የራስን ህይወት ለማቆየት ከሰማንያ በመቶ በላይ በሚቆጠረው ህዝብና በተሰበጣጠረ ኢኮኖሚ መስክ እዚህና እዚያ የሚመረተው ውስጣዊ ግኑኝነት የሌለው የአገራችን ኢኮኖሚ መልክ ሊይዝ የሚችለው ከሞላ ጎደል ላይ በተዘረዘረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዐይነት ብቻ ነው።

ከላይኛው አጭር ትንተና ስንነሳ የግዴታ የመርካንትሊስትን የኢኮኖሚ ፖሊሲን መከተል ይኖርብናል ማለት ነው። አንደኛ ፣ ለሰፊው ህዝብ የማይጠቅሙና ሰፊው ህዝብ ገዝቶ ሊጠቀምባቸው የማይችላቸውን የፍጆታ ዕቃዎች አይ እንዳሉ ማገድ ወይም ደገሞ ቀረጣቸውን በብዙ መቶ ፐርሰንት ከፍ በማድረግ እንዳይገቡ ማገድ ያስፈልጋል። በዚህ አማካይነት የሚተርፈውን ካረንሲ ለማሽን መግዢያ ማዋል ይቻላል። በሁለተኛ ደረጃ ፣ አገር ቤት ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በተመሳሳይ ምርት እንዳይዳከሙ እንደዚሁ የዕገዳ ፖሊሲ መከተል ሊታለፍ የማይችል ፖሊሲ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ፣ ወደ ውጭ የሚወጣና የሚገባን ካረንሲ በመንግሰት ቁጥጥር ስር በማዋል ኢንቬስት ለሚያደርጉ እንደአስፈላጊነቱ መሸጥ። በአራተኛ ደረጃ ፣ የውጭ ከበርቴዎች አገር ውስጥ ኢንቬሰት እንዲያደረጉ

የሚፈቀድላቸው በአንድ በኩል የሚተክሉት ኢንዱስትሪዎች አገር ውስጥ ለሚመረቱ የጥሬ ሀብትም ሆነ ሌሎች ምርቶች ገበያ ሲፈጥሩ ብቻ ነው። ከዚህም በላይ ፣ የተወሰነ የሶሻልና የአካባቢን ስታንደርድ የጠበቁ እንደሆነ ብቻ ነው። በተጨማሪም ፣ እንዴት ፣ ለማንና ምን እንደሚመረቱ በሚደረገው ውሳኔ ውስጥ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሊሳተፉ የሚችሉ ከሆነ ነው። ከዚህም በተረፈ ፣ በማንኛውም ኢንዱስትሪ ውስጥ ሆነ የአገልግሎት መሰጫ መስክ ሰራተኛው በሙያ ማህበር በየመስኩም ሆነ በአጠቃላይ የመደራጀት መብት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ነው። እነዚህን ቅድመ-ሁኔታዎች ብቻ የተቀበለ ወይም የሚያሟላ ኢንቬስት ማድረግ ይችላል።

ስለአንድ ህብረተሰብ ዕደገት በሚወራበት ጊዜ መነሳት ያለብን ከንጹህ የኢኮኖሚ ስሌት ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ከሁሉም አቅጣጫ እንዴት ማሳደግ ይቻላል የሚለውንም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ኢኮኖሚ መሰረታዊ ጥያቄ ቢሆንም ፣ የተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊኖር የሚችለው የባህልም ለውጥ ሲኖር ብቻ ነው። በአንድ በኩል የከተማዎች ጥበባዊ በሆነ መልክ መገንባት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በገጠርና በከተማ መሀከል የተዛባ ዕድገትና የባህል ልዩነት እንዳይኖር ማድረግ ለተስተካከለ ህብረተሰብአዊ ዕድገት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። ወደ ተጨባጩ የአገራችን ሁኔታ ስንመጣ ሁኔታውን በሶስት አቅጣጫ መቀየስ ወይም መመልከት ያሰፈልጋል። በመንግስት ደረጃ ሊወሰዱ የሚችሉ የኢንስቲቱሽን ለውጦች ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም ፣ የመንግስትን ሚና ከማዕከላዊ አገዛዝ ጀምሮ በአውራጃና በወረዳ እንዲሁም በሎካል ደረጃ በግልጽ ማሰፈር ለኢኮኖሚውም ሆነ ለህብረተሰብአዊ ለውጥ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። በሁለተኛ ደረጃ ፣ በግል እንቅስቃሴ ሊሰሩ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በሃሳብና በዝቅተኛ ክሬዲት መርዳትና መደገፍ ለዕድገት አመቺን ሁኔታ ይፈጥራል። እዚህ ላይ ያልተንዛዛን የግል ሀብት ሚናን በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በአንድ በኩል በመሬት ላይ ሊኖር የሚችል የአጠቃቀም ዘዴንና ራሱ ከበርቴ ነኝ የሚለው በራሱ ሀብት እየገዛ በሚተክለውና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ በሚያሳትፈው የኢንዱስትሪ ሀብት መሀከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ማሰቀመጥ ከቀረጥና ከዋጋ ትመና አንፃር ሊወሰዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት ለዕድገት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። በሶስተኛ ደረጃ ፣ በህብረት ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎችን በፋናንስ ስለ መደጎምና ለረዥም ጊዜም ቋሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ዕድገትን ያፋጥናል። አንድ በኢኮኖሚ መጽሀፎች ውስጥ የሰፈረና ብዙ የሶስተኛውን ዓለም ህዝቦች ያሳሳተ የኢኮኖሚ አመለካከት አለ። ይኸውም ካፒታሊዝምን የየግለሰቦች ድርጊት ውጤት አድርጎ መውሰድ ነው። በታሪክ እንደታየው በአውሮፓ ውስጥ የተሰሩት ድልድዮች ፣ ካናሎች ፣ የገበያ ቦታዎችና ከተማዎች እንዲሁም ቤተ መንግሰትና ካቴድራሎች በነፃ ገበያ አማካይነት ሳይሆን ሰፊውን ህዝብ በማንቀሳቀስና በማሰማራት ነው። ስለዚህም ፣ በኛም አገር ሰፊውን ህዝብ ለተለያዩ ሙያዎችና የስራ መስኮች ማንቀሳቀስና ማሰማራት ሊታለፍ የማይችል ጉዳይ ነው። ካለሰፊው ህዝብ ተሳትፎ ሰፋ ያለ ህብረተሰብአዊ ሀብት መፍጠርና ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት በፍጹም አይቻልም። ይህንን ለማድረግና የተትረፈረፈውን የሰው ኃይል ለመጠቀም ራሱን የቻለ ልዩ የገንዘብ ፈንድ መፍጠርና ፣ ልዩ ከሆነ የክሬዲት ሲስተም ጋር ማገናኘት ለኢኮኖሚው ልዩ ውስጣዊ-ኃይል ይሰጠዋል። ለዚህ ደግሞ ወሳኙ የፖለቲካ ጥያቄ መፈታት ሲኖርበት ፣ አገር ውስጥ ባለው ሀብትና መሳሪያ ተዓምር መስራት ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር ግን ከዚህ የሃሳብ ውዥንብርነት መላቀቅና ሳይወናበዱ ለአንድ ዓላማ ቆርጦ መነሳት ነው። ለአገራችን የተወሳሰበ ችግር ያለው አማራጭ መፍትሄ ይህ ብቻ ነው።

ወደ መጨረሻው ጥያቄ ልምጣና ፣ የኔ ዕምነትና ትግል በግራና በቀኝ ተብሎ ሊወሰን የሚችል ዐይነት አቋም አይደለም። ከርዕዮተ-ዓለም ነፃ የሆነ በተለይም ደግሞ ዕውቀትን ያስቀደመ ህብረተሰብአዊ ትግል ብቻ አንድን ህዝብ የዕውነተኛ ነፃነት ባለቤት ያደርገዋል የሚል ዕምነት አለኝ። አንድ ህዝብ ዕውነተኛ ነፃነቱን ሊቀዳጅ የሚችለው ያለውን የተደበቀና ተፈጥሮአዊ የማሰብ ኃይል ሲጠቀም ብቻ ነው። ስራን ሳይንቅ ለስራ በጋራ ታጥቆ ሲነሳ የሚኖርበትን የተከበረ አገር መመስረት ይችላል። ለዚህም ሃላፊነትን መረዳትና የተሰጠን ተግባር በስነ-ስርአት ማጠናቀቅ ለብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ እጅግ አስፈላጊ ነው። ለጊዜያዊ ጥቅም ተብሎ የሚካሄድ የችኮላ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እጅግ አደገኛና ህብረተሰብአዊ ሀብትን የሚያባክን ነው። ሰለዚህም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሰፋ ያለ መሆን አለበት። በአንድ መስክ ላይ የሚደረግ ኢኮኖሚያዊ ርብርቦሽ አንድን ህብረተሰብ ካለበት ሁኔታ በፍጹም ሊያወጣው አይችልም። ይህም ማለት ሰፋ ያለ የስራ ክፍፍል መዳበር ለዕውነተኛ ሀብት መሰረታዊ መንገድ ነው። ከዚህ በተረፈ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ስትራቴጂያዊም መሆን አለበት። በኛም ሆነ በሌሎችም አፍሪቃ አገሮች ያለው ችግር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንድ ህብረተሰብ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ በሚወድቅበት ጊዜ ሊያወጣው ወይም ሊከላከው የሚችል አይደለም። በሌላ አነጋገር ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ቢኖር ፣ የውሃ ሙላት ቢመጣ ፣ ቃጠሎ ቢፈጠርና ሌሎችም አገርንና ህዝብን ሊጎዱ

የሚችሉ አደጋዎች ቢፈጠሩ ህዝቡን ሊከላከሉም ሆነ ከአደጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያወጡት የሚችሉ መሳሪዎችና ቁሳቁሶች የሉም። የእሳት አደጋ መኪናዎች ፣ ውሃ ከላይ ሆነው ሊረጩ የሚችሉ ሄሊኮፕተሮች ፣ የቆሸሸን ውሃ ቶሎ አጣርተው ለተጠቃሚው ሊያቀርቡ የሚችሉ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች የሉንም። የህክምና መሳሪዎችን ብቻ ሳይሆን ከአገራችን ሁኔታ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ትናንሽና ትላልቅ ሆስፒታሎች እንደልብ የሉም። አስፈላጊውም መድሃኒት አይገኝም። ስለዚህም ህዝባችን ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠ ነው ማለት ነው። ስለ ኢኮኖሚ ግንባታ ስናወራ ከዚህ ስትራቴጂክ ሁኔታ መነሳት ያለብን ይመስለኛል። ይህንን ስናደርግ በእርግጥም ስለኢኮኖሚና ስለህብረተሰብ ዕድገት ማውራት እንችላለን ማለት ነው። በመሆኑም የኔ አቋም ከጠቅላላው ህዝብ አንፃር መታየት ያለበት ሲሆን ፣ የሰፊው ህዝብ መብት መጠበቅና በማንኛውም ዲሞክራሲያዊ ህይወት ተሳትፎ መካፈልን እንደመሰረታዊ ጉዳይ የሚመለከትና ለዚህም የሚታገል ነው። ለዚህ ሁሉ ስልጣኔ የሚለው መሰረታዊ ጽንሰ-ሃሳብ ጠቅላላውን የህብረተሰብ ክፍል ያካተተ ሆኖ መታየት እንዳለበት አምናለሁ። መልካም ንባብ !!

**ፈቃዱ በቀለ**

**fekadubekele@gmx.de**